# 5S ፋውንዴሽን

5S ፕሮጀክት በብራይተን እና በሰሴክስ ሜዲካል ትምህርት ቤት (BSMS) በአለም አቀፍ ጤና እና ኢንፌክሽኖች ትምህርት ክፍል (GHI) ከምስራቅ እና ደቡባዊ አፍሪካ የማህበራዊ ሳይንስ ምርምር ድርጅት (OSSREA) ጋር በመተባበር እየተተገበረ የሚገኝ የምርምር ፕሮጀክት ነው። ፕሮጀክቱ በኢትዮጵያ ውስጥ በስፋት በሚገኙ ሁለት ዓይነት የቆዳ በሽታዎች ማለትም ተላላፊ ያልሆነ ዝሆኔ ወይም የእግር እብጠት እና እከክ ላይ ትኩረት በማድረግ ይሠራል። የፕሮጀቱ ዋነኛ ዓላማ የማህበራዊ ሳይንስ እይታዎችን በመጠቀም በተጠቀሱት በሽታዎች አማካኝነት የሚስተዋሉ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ሥነ-ልቦናዊ ችግሮችን እና መገለሎችን ማጥናት ነው።


**ፕሮፌሰር ጌትነት ታደለ**
**(ፕሮጀክት መሪ)**

getnett2001@yahoo.com

www.ossrea.net

+251111239484

5S Foundation Ethiopia



SUPPORTED BY NIHR | National Institute for Health and Care Research

UKaid from the British people




# እከክ
## (የእከክ በሽታ)


ይህ መልክት በአማራ ህ/ሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የህ/ስብ/ጤና/አደ/መከ/መቆ/ ዳይሬክቶሬት የእከክ ወረርሽኝን ለማከምና ለመቆጣጠር ከተዘጋጀ አጭር የስራ መመሪያ ተወስዶ በ5S ፋዉንዴሽን የተዘጋጀ ነዉ።



## የእከክ በሽታ ምንነት እና የሚተላለፍባቸው መንገዶች

እከክ በአይን በማትታይ የሰዉን የቆዳ ክፍል ቦርቡራ በምትገባ ቅንቅን /ረቂቅ ተዋስ/ የሚመጣ ተላላፊ በሽታ ነው። ተህዋሷ/ቅንቅኗ/ የቆዳችንን ክፍል ቦርቡራ ከገባች በኋላ በሰውነት ክፍል ትኖራለች፤ እንቁላሏን በመጣልም ትራባለች።

የእከክ በሽታ ረዘም ላለ ጊዜ በቆየና ቀጥተኛ በሆነ የቆዳ ለቆዳ ንክኪ ይተላለፋል። በተጨማሪም በጋራ በሚጠቀሟቸው አልባሳት፣ ፎጣዎች፣ የሌሊት ልበሶች፣አንሶላዎች ሊተላለፍ ይችላል።

## ለእከክ ወረርሽኝ ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች

እከክ ማንኛውንም የህብረተሰብ ክፍል የሚያጠቃ ቢሆንም የሚከተሉት የበለጠ ተጋላጮች ናቸው።

- በምግብ እጥረት የተጎዱ
- ረዥም ጊዜ ከሌሎች በሽታዎች ጋር የሚኖሩ የህ/ሰብ ክፍሎች
- ዉሃ አጠር በሆኑ አካባቢዎች የሚኖሩ ማህበረሰቦች እና የግል ንጽህናቸውን የማይጠብቁ ሰዎች
- በተፈጥሮ አደጋ የተጎዱ የህ/ሰብ ክፍሎች
- ተጠጋግተው የሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች (የቆሎ (የአብነት) ተማሪዎች፣ በትምህርት ቤቶች፣ በማረሚያ ቤቶችና በስደተኞች ካምፖች የሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች



## የእከክ በሽታ ምልክቶች እና የሚታይባቸዉ የሰዉነት ክፍሎች

ተህዋሷ ወደ ሰው ሰውነት ከገባች በኋላ የበሽታው ምልክቶች የሚታዩበት ጊዜ ከሰው ሰው ይለያያል። ለመጀመርያ ጊዜ ለበሽታው በሚጋለጡ/በሚታመሙ/ ሰዎች ከ2 - 6 ሳምንታት የሚፈጅ ሲሆን ለ2ኛ ጊዜ ወይም በተደጋጋሚ ለበሽታው በሚጋለጡ ሰዎች ከ1- 4 ቀናት ውስጥ የበሽታው ምልክት (ማሳከክ) ሊጀምር ይችላል። ብዙ ግዜ ከባድ የሆነ የማሳከክ ስሜት/በሌሊት የሚብስ/ እና ሽፍታ/ ሽፍፍ ያሉ እባጮች/ ይታያል። በተጨማሪም ውሃ ወይም መግል የቋጠሩ ትንንሽ አባጮች እና የተቦረቦረ ቆዳ ሊኖር ይችላል። የበሽታዉ ምልክቶች የእጅ እጣቶች መገናኛ፣ የእጅ አንጓ፣ ክርን፣ ብብት፣ ጡት፣ ወገብ፣ መቀመጫ/ቂጥ/ አካባቢና ጉልበትና ብልትን ያጠቃል። ተገቢው ህክምና ከተሰጠ በኋላ እነዚህ ምልክቶች በተለይም ማሳከኩ ከ3 - 4 ሳምንታት ሊቆዩ ይችላል።

## የእከክ በሽታ የሚያስከትላቸዉ ጉዳቶች

- ያለማቋረጥ ሰዉነትን ማከክ
- እንቅልፍ ማጣት
- የሰዉነት መቁሰል
- ከትምህርት ወይም ከስራ መስተጓጎል
- በጊዜዉ ያልታከመ የእከክ በሽታ ለተጓዳኝ ችግሮች እነድ ኢንፌክሽን፣ የልብ በሽታ፣ የኩላሊት ችግር ሊዳርግ ይችላል
- ከተለያዩ ማህበራዊ መሰባሰቦች (ለምሳሌ ለቅሶ፣ ሰርግ፣ ማህበር፣ ሰንበቴ፣ ትምህርት፣ የእምነት ቦታዎች ወዘተ መገለል) ፡ ኢኮኖሚያዊና ሥነ-ልቦናዊ ተፅዕኖዎችና የመሳሰሉት ያስከትላል

## የእከክ በሽታ ህክምና እና መከላከያ መንገዶች

- የግል ንጽህናን መጠበቅ፤ ገላን እንዲሁም ልብሶችን በሳሙና ማጠብ
- በሽታዉ በጀመረ ጊዜ ባፋጣኝ ወደ ጤና ጣቢያ በመሄድ ህክምና ማግኘት
- በበሽታዉ ከተያዘ ሰዉ ጋር ቀጥተኛ የሆነ ንክኪ ማስወገድ
- በሽታዉ ከያዘዉ ሰዉ ጋር ግንኙነት ያላቸዉ ሰዎች በሙሉ መላዉ ቤተሰቡን ጨምሮ ህክምና ማግኘት ይኖርባቸዋል
- ህክምና ከተጀመረ በኋላ ልጆችን ቢያንስ ለአንድ ቀን ከትምህርት ማስቀረት ያስፈልጋል
- የእከክ በሽታ በህክምና የሚድን ሲሆን ህክምና ከተጀመረ በኋላ በጤና ባለሙያ የታዘዙትን መድሃኒቶችም በአግባቡ መዉሰድ